# አረ ጎበዝ!! ለውጡን ለውጥ እናርገው

ተስፋሁን አረጋይ

ኢትዮጵያዊያን ለኢትዮጵያዊነት ያላቸውን ክብርና ፍቅር ይሄ ነው በማይባሌ ስሜት ሲገሌጹ መታየታቸው ለተወላጆቹ ብቻ ሳይሆን ለመላው የዓለም ህዝብ የሚያስደንቅ ትእይንት ሆኖ እየታየ ነው። ከዚህ በፊት አንዳንድ በብሄር (በዘር) ተደራጅን የሚሉ ሃይሎች በኢትዮጵያውያን ማህል ከፍተኛ “የብሄር ቅራኔ” አለ ከማለት አልፈው የአንዳንድ ብሄር ተወላጆች የሌላውን ብሄር ተወላጆች በመሪነት የመቀበል ችግር አለባቸው እያሉ አንዳንድ ብሄሮችን በተለይ የአማርኛ ተናጋሪውን ስም ሲያጠቁሩት ቆይተዋል። ያለፉት ወራት ግን ይህን ከንቱ የጥላቻ ቅስቀሳ የሚያረክስ ስራ የታየበት ወቅት ነው። ዶ/ር አብይ አህመድ የህዝብን የልብ ትርታ በማድመጥ የህዝብን ጥያቄ በማንሳት ከስልጣን ከመዉጣታቸው በፊትም ሆነ ከስልጣን ከወጡ በኋላ በመላው የኢትዮጵያ ህዝብ በተለይም በአማርኛ ተናጋሪው ህዝብ ያገኙት ድጋፍ በታሪካችን ከፍተኛ ተወዳጅ መሪ እንዲሆኑ አድርጋቸዋል። ኢትዮጵያዊነቱን የሚወደው ሀይል ሁሉ የዶ/ር አብይ ከኦሮሞ ብሄር መምጣት ጉዳዩ አልሆነም ያውም ከትልቁ ብሄር(ከነ አብዲሳ እና ጃጋማ)በመወለዳቸው ኢትዮጵያዊያን እንዲኮሩባቸው አደረጋቸው እንጅ ማንነታቸው ለጥያቄ አልገባም። ከዚህም አልፎ ዶ/ር አብይ በህዝብ ላይ ብዙ ግፍ የሰራው የኦህዴድ/ኢህአዴግ አባል እና መሪ ሆነው ሳለ ይህን የተሰራ ግፍ በማዉገዛቸውና ይቅርታ በመጠየቃቸው ህዝብ የይቅርታ ልቡን ሰጣቸው እንጅ ቂም ቆጥሮ ፊቱን አላዞረባቸውም።በዚህም የኢትዮጵያ ህዝብ ሁለት ነገሮች አረጋግጧል።

1ኛ በመሪነት የሚቀበላቸው ሰዎች ድጋፍና እምነት የሚለካው በመጡበት ዘር ውይም ብሄር ሳይሆን ለኢትዮጲያና ለህዝቡዋ ባላቸው ፍቅር እና ለሃገሪቱ ሉአላዊነትና ለህዝቡዋ የእኩልነት መብት መከበር በሚያከናዉኑት ተግባራዊ እንቅስቃሴ መሆኑን፤

2ኛ የኢትዮጵያ ህዝብ አንድን ድርጅት የሚቀበለው በሚከተለው ህዝባዊ መስመርና ተግባራዊ ለማድረግ በሚቀርጻቸው ፖሊሲዎች ላይ ተመስርቶ መሆኑን፤ ለዚህም ወያኔ /ኢሃአዴግ ጋር የተካሄደው ትግል አቶ መለስን ወይም ወያኔ /ኢህአዴግን በጭፍን በመጥላት ሳይሆን አቶ መለስና ድርጅቶታቸው አገሪቱን የሚያፈርስ ህዝብዋን የሚያፋጅ መርዝ በመዝራት የሚታወቀው ፖሊሲያቸውን በህዝብ ሊይ በመጫን ከፍተኛ ጭቆናና እመቃን ሲያደርሱ በመቆየታቸው መሆኑን ይሄው ታሪክ ፍንትዉ አድርጎ አሳየን። ዛሬ እራሱ ኢህአዴግ የሚመራት ኢትዮጲያ ለዜጎችዋ የመከራና ስቃይ ቤት ሆና መቆየትዋን እራሳቸው የኢህአዴግ ሰዎች እየነገሩን ነው።

እንግዲህ የኢትዮጲያ ህዝብ ኢትዮጵያዊ ለሆነ መሪ ህዝባዊ ለሆነ የፖለቲካ መስመር ልቡ ክፍት መሆኑን በየአደባባዩ እየወጣ ካሳየ በኋላ ይህን በከፍተኛ መስዋህትነት በመገኘት ላይ ያለውን የለዉጥ ጉዞ እንዳይጨናገፍ የለውጡ ሃይል በመሆን እያንዳንዱ ዜጋ እና የፖለቲካ ድርጅቶች ድርሻቸውን መወጣት ይኖርባቸዋል።ታዲያ ከዚህ አንጻር እየታዩ ያሉትን አንዳንድ ክፍተቶች እና ጉድለቶችን በማሳየት እነዚህንም በፍጥነት ለማረም ሁላችንም እንድንረባረብ እጠቁማለሁ።

1ኛ እንደምናስታውሰው ደርጎች በስልጣን ላይ የተደላደሉት የንጉሱን ስርዓት ደካማ ጎኖች አጉሌተው በማሳየት የህዝቡ መብት እና ጥቅም ተነክቷል እያሉ በመንቀሳቀስ የህዝቡን ስሜት ከተቆጣጠሩ ቦኋላ በተለይ “የመሬት ላራሹን” ጥያቄ መልሰናል ካሉ ቦኋላ ነው። በዚህ ወቅት በቂ ልምድ በሌላቸው የኢትዬጵያ የፖለቲካ ሊቆች ማህል ከፍተኛ የሆነ ውዠንብር ፈጥሮ ነበር፤ በተለይ ደግም የፖለቲካ ድርጅት አቋቁመናል በማለት በውጭ ይንቀሳቀሱ ከነበሩት ቡድኖች ውስጥ ከፊሉ ይህን “ተራማጅ” መንግስት እንደግፋለን በማለት ወደ ሃገር ቤት ገብተው ከደርግ ጎን ተሰልፈው መስራት ሲጀምሩ ሁሉም ነገር ተበላሸ። እነዚህ ሃይሎች ከደርግ በፊት ከሚያውቁዋቸው በትግሉም ውስጥ ከቆዩት ሃይሎች ጋር ረጋ ባለ መንፈስ ተወያይተው በጋራ በመስራት የጋራ አቋዋም መያዝ ሲገባቸው በጠመንጃው ከሚተማመነው ደርግ ጎን በመቆማቸው ያን ሁሉ ወጣት አስጨረሱ፤ እነዚህ ሃይሎች እንኳዋንስ ለህዝብ ሊጠቅሙ የሚወዱዋቸውን መሪዎቻቸውን በደርግ አስበልተው ድርጅታቸውንም ከጥቅም ውጭ አደረጉ። ወያኔ/ኢህአዴግም ስልጣን ሲይዝ በተመሳሳይ መልክ ከውጭ እየበረሩ ገብተው ከፊትም ከኋላም የተሰለፉት ሃይሎች ላለፉት 27 ዓመት መከራችን አስተዋጽኦ አድርገዋል። ዛሬም ተመሳሳይ እድል እንዳይገጥመን እፈራለሁ፤ በተለይ በውጩ ዓለም በትግል ላይ የቆዩት ድርጅቶች በመቀራረብ ቁጭ ብለው በመወያየት ልዩነታቸውን አጥብበው ቢቻል መዋሃድ ባይቻል በኅብረት(በግንባር) መስራት ሲገባቸው ይህ ካልሆነ ደግሞ የሚስማሙባቸውን የጋራ ሃገራዊ አጀንዳዎች አቅርበው ሁሉም ድርጅቶች ሊገዙለት የሚገባ የጋራ መርህ(ሰነድ) በማውጣት አንዱ የአንዱ ጠላት ሳይሆን አጋር መሆኑን በመተማመን ሰብሰብ ብለው ወደ ሀገር ቤት መግባት ሲገባቸው በየፊናቸው በተናጠል ከኢህአዴግ ኢምባሲ ጋር በመደራደር ቀድሞ አለሁ ለማለት የሚያደርጉት እሩጫ በጣም አደገኛ ነው። አንዳንድ ድርጅቶች እራሳቸውን ትልቅ አድርገው በማየት ሌሎቹን የሚንቁ ከሆነ ተሳስተዋል፤ አንዳንዶች ደግሞ ከነሱ ውጭ የሆነውን ሃሳብ ለመስማትና ለመቀበል የተዘጋጁ ካልሆኑ አሳፋሪ ነው።

ታድያ እንደዚህ ዓይነት ስህተቶች በየጊዚየው በታሪካችን እየተደጋገሙ ሲያዳክሙን እየታየ ህዝብ ዝም ማለት የለበትም፤ የድርጅቶቹ አባላትም እነዚህን የሚጋልቡ መሪዎቻቸው ልጓም ሊያበጅላቸው ይገባል፤ ይገባኛል የአንዳንድ ድርጅቶች

መሪዎች አይዋደዱም ወይም አይፈላለጉም ትግሉ ግን ከግለሰቦቹ በላይ በመሆኑ የድርጅቶቹ አባላት ተጽእኖ ማሳደር አለባችሁ። የመገናኛ ብዙሃንም ዜናዎችን ከማናፈስ አልፈው የተለያዩ ድርጅቶችን መሪዎች በአንድ መድረክ ላይ በማቅረብ በሚካሄደው ውይይት የዚህን ችግር መንስኤ ህዝብ እንዲያውቅ የማድረግ ሃሊፊነት አለባችሁ። ይህ ትግል ከዚህ ደረጃ እንዲደርስ የተከፈለው መስዋእትነት ክብደት ምን ያህል እንደሆነ ሁላችንም እናውቀዋለን፤ ታዲያ ፖለቲካውን ለመምራት የሚሮጡት ሃይሎች በሚሰሩት ስህተት ይህ የረዢም ጊዜ ትግል ውጤቱ ከተበላሸ የሚያስከትለው መስዋዕትነት መለኪያ የለላው በመሆኑ ዝም ብሎ መቀመጥ አይቻልም።
በተመሳሳይ መልክ በሃገር ቤት ያሉት ተፎካካሪ ድርጅቶች እስካሁን ሰብሰብ ብለው ሲንቀሳቀሱ በጋራ መግለጫ ሲሰጡ ባለማየታችን ያሳዝናል፤ አሁን የተከፈተው እድል በመቀራረብ በሰፊው በመወያየት እየተቻቻላችሁ የምትስማሙበት ጊዜ እና ቦታ የሚሰጥ በመሆኑ ይህን አጋጣሚ ካልተጠቀማችሁበት ድርጅታዊ ህልውናችሁ እንዲያከትም እንደተስማማችሁ ይቆጠራል፤ ስለዚህ ዛሬ የአስቸኳይ አዋጁን አታመካኙም ፖሊስ እና ደህንነትም ተንፈስ ብሎአል፤ እባካችሁ አጋጣሚውን በአግባቡ ተጠቀሙበት፤ ሰብሰብ በማለት ጠንካራ ሃይል መፍጠር የሚቻልበት ወቅት አሁን ነው፤ በመንቀሳቀስ ከህዝብ ጋር የምትተዋወቁበት እና የምትዋሃዱበት እድል ተከፍትዋል ተጠቀሙበት፤ እስከ መቼ ኢህአዴግ እንደቀለደባችሁ ትኖራላችሁ፤ ከናንተ ብዙ ጸጋ ስንጠብቅ የኢህአዴግ ምጽዋት ተቀባይ እንዳደረጋችሁን ምን ያህል ተገንዝባችሁታል?

2ኛ ሌላው ለዚህ ትግል ከፍተኛ ጉልበት ነው ብዬ የማምንበት ሃይል የመገናኛ ብዙሃንን ነው(TV፣Radio, Website and Social Media የመሳሰሉት) ብዙዎቹ የመገናኛ ብዙሃን በተለይ አገር ቤት ያሉት ዶ/ር አብይ ከስልጣን ከወጡ ቦኍዋላ የሃገሪቱን ልጆች ብሶት እና መከራ በሰፊው ሲዘግቡ ይሰማል እኛም የማናውቀውን እንደሚነገሩን በቁጨት እንደገና እያለቀስን አይናችን ተክለንባቸው እንውላለን፤ ግን እነዚህ የመገናኛ ብዙሃን ዞረው ዞረው “ኢህአዴግ በተሃድሶ ችግሮቹን ሁሉ እየፈታ ነው” ይሉናል፤ አንዳንዶቹ ደግሞ “ዶ/ር አብይ እንዲህ ማድረግ አለበት” ከማለት አልፈው አይሄዱም። ሁለም የመገናኛ ብዙሃን ካሰባሰቡት መረጃ ተነስተው ኢህአዴግ አገር ለመምራት ብቃት ያለው ድርጅት አይደለም አይሉንም። እንዲያውም ይባስ ብለው በአንድ ወቅት በግል ድክመታቸው ከነአቶ መለስ ጋር በመኮራረፍ ከኢህአዴግ የተባረሩትን “መሪዎች እና ጀኔራልች” በየመድረኩ በማቅረብ ሰፊ እድል ሲሰጡዋቸው እና በኢህአዴግ ጥገና ውስጥ ቦታ እንዲያገኙ ሲያመቻቹላቸው ይታያለ። ለምሳሌ ያህል በ TV በሚተላለፈው የፓርላማ ስብሰባ ቀርቦ የራሱን ልክስክስ ባህሬ(በሴት እና በንዋይ ፍቅር) ያጋለጠው አቶ ታምራት ላይኔ በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን ሲሰጠው የምናየው እድል ከዚያም አልፎ በአቶ ኢሳያስ አቀባበል የክብር እንግዳ መሆኑ የሚገርም ነው። አቶ ታምራት ሀገርን እና ህዝብን በመካድ አሁን ለደረስንበት ውድቀት ካደረሱን ጥቂት ሰዎች አንዱ ሲሆን በተለይ ደግሞ በአማራው ህዝብ ላይ ለተፈጸመው ጭፍጨፋ እና የኢትዮጵያን ኦርቶድክስ ቤተክርስትያን ለማፈራረስ በተወሰደው እርምጃ ትእዛዝ ሰጭ እና ትእዛዝ አስፈጻሚ ሆኖ ይህን ሁለ መከራ እንድንቀምስ በማድረጉ ላይ የተጫወተው ሚና እንዲሁ በቀላሉ የሚረሳ አይደለም። ከእስር ሲወጣ ግለሰቡ በጣም ብልጣብልጥ በመሆኑ የወንጌሊዊት ቤተክርስትያንን እንደመከለያ አድርጎ ለመረማመጃነት ይጠቀምባት እንጅ የሰራውን በደል ሁሉ በግልጽ አስቀምጦ ይቅርታ አልጠየቀም፤ በአሜሪካ ሲኖር ይህን ያህል ዘመን ያሰቃያቸውን አባ መርቀሪዎስ እና ስደተኞቹን አባቶች ይቅርታ ሳይጠይቅ “የመጽሃፍ ቅዱስ ሰባኪ” ነኝ እያለ የተዝመነመነ ህይወቱን ሲቀጭ ቆይቷላ። አሁንም ለመገናኛ ብዙሃን እራሱን እያመቻቼ ብቅብቅ ሲያደርጉት ሁለት የሞቱ ሰዎችን (ክንፈን እና መለስን) እያነሳ ከመውቀስ አልፎ ዛሬም በስልጣን እና በህይወት ያሉትን ወንጀለኞች የሰሩትን እና በመስራት ላይ ያሉትን ጉድ ደብቆ ለመያዝ ሲሞክር ይታያል። እንግዲህ አቶ መለስን በማጀብ እንደ እነ ታምራት፤ ጻድቃን እና አበበ የመሳሰለት ኢትዮጵያን ከዚህ አደጋ ያስቀመጥዋት የትላንት የኢህአዴግ መሪዎች እና የድሮ የኢህአዴግ ወዳጆች ከውጭም ከውስጥም እየተጠራሩ በመገናኛ ብዙሃን ልዩ እድል ሲሰጣቸው በማየታችን በመገናኛ ብዙሃን ዙሪያ ያለውን ሰፊ ድክመት የበለጠ አሳይቶናል። ስለዚህ የመገናኛ ብዙሃን ታሪክን ይቅርታ በመጠየቅ አቅጣጫችሁን ቀይሩ፤ ለዘመናት እድል ለተነፈጉት የኢትዮጵያ ሙሁራን እና ተደፍቀው ለኖሩት የተፎካካሪ ድርጅቶች እድሉን ስጡዋቸው፤ እነዚህን ሃይሎች ህዝብ እንዲያውቃቸው አዲስ እና የተሻለ አቅጣጫ እንዲያሳዩን መድረኩን አትንፈጉዋቸው፤ ይህን ካላደረጋችሁ ይህ ሞቅሞቅ ሲበርድ ለናንተም ህልውና አደጋ አለው።

3ኛ አዎ በድርጅቶች መካከል የሚፈጠረውን መቀራረበ ሁላችንም እንወደዋለን ሆኖም ግን አሁንም የምንቀራረበው “በብሔረሰብ’ (በዘር) አመጣጣችን አንድ አይነት በመሆናችን ከሆነ ያው ወደ ከረምንበት ጭቃ ተመልሰን መግባት ነው። በመቀሌ ኮንፈረንስ ያየነው ይሄንኑ ነው፤ ምንም እንኳን አይጎዱንም ያሉዋቸውን አቶ ሌደቱን ጎልተዋቸው ቢሰነብቱም(ቋንቋውን ስለማይሰሙ) ተሰብሳቢዎቹ የቀጠሉ እና ያቋረጡ የወያኔ ሃርነት አባላት ናቸው። ሰብሰባወም በዋነኛነት ወያኔ ሀርነት ትግራይ ከገባችበት አዘቅት እንዴት ትውጣ፤ እንደገና እንዴት እንጠናከር በሚሉት ሀሳቦች ላይ ያተኮረ ሲሆን ከዚያ ሲያልፍ ደግም አሁንም ትግራይን ብቻ ነጥሎ በማየት የትግራይን ጥቅም ማስከበር በሚል ፈሊጥ በተለመደው እብሪት በሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ ህይወት ላይ ለመረማመድ የሚደረጉ ዲስኩሮች እና ዛቻዎችን ሲያስተናግድ የሰነበተ ዱለታ ነበር። በዚህ ስብሰባ የትግራይ ህዝብ በሌሎች ኢትዮጵያውያን ወገኖቹ ላይ ጥርጣሬ እና

ሲጋት እንዲያድርበት የሚያደርጉ የተሳሳቱ መረጃዎች ይረጭለት ነበር። በጣም የሚገርመው ሲያዋርዱት ግፍ ሲፈጽሙበት የቆዩትን ህገ መንግስት ሰሞኑን ተጣስብን ይከበርልን እያሉ መፈክር መያዛቸው ነው። በዚህ ስብሰባ ከዚህ በፊት በሃሳብ የተለዩዋቸውን ወገኖች በሞቱት የትግራይ ሴጆች አጽም በመማጸን በይቅርታ ተቀራርበው ጠንካራ የትግራይ ሴጆች ሃይል እንዲፈጠር ከመለመን አልፈው በሰሩት ስህተት የበደሉትን የኢትዮጵያ ህዝብ እና አገሪቱን ይቅርታ ሲጠይቁ አልተሰማም፤ የትግራይንም ህዝብ አሁንም የቁም እስር አድርገው በብቸኝነት ለመግዛት ባላቸው የታጠቀ ሰራዊት ሲኩራሩ ተሰሙ እንጅ በጥፋታቸው አልተጸጸቱም። ታዲያ ይህ ሲሆን እንደ እነ ዶ/ር አረጋዊ በርሄ አይነቶቹ በጣም ጥቂት የትግራይ ልጆች ይህን ደባ ቢቃወሙም ብዙሃኑ የትግራይ ሙህራን ድምጻቸውን አጥፍተው ትግራይን ወያኔ ሀርነት ሲያዋርዳት እና ህዝቡን ከወገኖቹ ነጥሎ ከከፍተኛ አደጋ ላይ ሲያስቀምጠው ዝም ማለታችሁ በታሪክ ከማስወቀስ አልፎ በግል ህይወታችሁም በህፍረት እየተሸማቀቃችሁ እንዴትኖሩ ያደርጋችኋል። ስለዚህ የትግራይ ልጅ ነኝ የምትሉ ሁሉ በድፍረት ወጥታችሁ የለውጡ አካል መሆን አለባችሁ።

በተመሳሳይ መልክ በኦሮምኛ ተናጋሪዎቹ ድርጅቶች ዙርያ የምናየው መሳሳብ በአብዛኛው ቋንቋን መሰረት ያደረገ በመሆኑ ስጋትን እየፈጠረብን ነው፤ በዚህ ትግል የኦሮምኛ እና የአማርኛ ተናጋሪ ወጣቶች ጀግንነት የማይዘነጋ ቢሆንም ሁሉም የኢትዮጵያ ልጆች መስዋእትነት እንደከፈሉ መስዋእትነቱንም ከባድ ያደረገው በብሄር በተከፋፈለ ትግል ውስጥ በመግባታችን መሆኑን መሪዎቻችን ጠንቅቀው ያውቁታል። ግን አሁንም ተመልሰን መጀመሪያ ብሄራችን እናጠናክር የምንል ከሆነ ውጤት አልባ ስህተትን መደጋገም ብቻ ሳይሆን መጥፎ ውጥረት እንፈጥራለን። የሚንሰታውን ስህተት ንቀን ብናልፈውም አዲስ አበባ በሚሌንየም አዳራሽ አቶ ጁሃርን ለመቀበል በተደረገው ድግስ አዳራሹ በኦነግ(OLF) ሰንደቅ አላማ አሸብርቆ አንድም የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ አለመኖሩ ያስተላለፈው መልእክት ጥሩ አልነበረም፤ በተመሳሳይ ሁኔታ አሁን ከውጭ እየገቡ ያሉት ኦሮሞ ቀመስ ድርጅቶችም ሆነ ታዋቂ ግለሰቦች ትኩረታቸው በኦሮምኛ ተናጋሪዎች ዙሪያ በመሆኑ ጉዳዩ አሳሳቢ ነው። ከኦነግ(OLF) ጋር አስመራ ለመደራደርም በዋነኛነት የተላኩት ኦሮምኛ ተናጋሪዎች በመሆኑ ብዙ ጥያቄ ያስጭራል፤ ከሌሎቹ ብሄሮች ተወላጆችም ይህ ድክመት የሚታይ በመሆኑ ቶሎ ሚዛኑን ካላስተካከልነው አደገኛ ነው፤ ችግራችን ሃገር አቀፍ ስለሆነ ሀገር አቀፋዊ መድረኮችን በማስፋፋት ህዝቡን በማቀራረብ መተማመንን በመፍጠር የቆሰለውን ኢትዮጵያዊነት እንዲያገግም ካላደረግን የሁሉንም ዜጋ ሙብት የሚያስከብር ዴሞክራሲያዊ ስርዓት መገንባት አንችልም።

ከዚህ አንጻር እነ ዶ/ር አብይ ይሄን ያድርጉ ለምን ይሄን አላደረጉም እያልን ከዳር ቁጭ ብለን “ተደምረናል” በማለት ብቻ ውጤት የምንጥብቅ ከሆነ መቀለድ ይሆናል፤ ደግሞ መዘንጋት የሌለብን እነ ዶ/ር አብይ ቅን ልቦና አላቸው ብንልም የተከበቡት እና የሚመሩት ኢህአዴግን ከነግሳንግሱ ነው። ስለዚህ ልናዝንላቸው ይገባል ስንቱን ማጽዳት ይችላሉ? እኔስ እንደ ሚካኤል ጎርባቾብ እንዳይሆኑ እፈራለሁ፤ ጎርባቾብ የሶብየት ኮሚኒስት ፓርቲ አምባገነናዊ አገዛዝ እንዲያከትም እና ህዝቡ የተሻለ ህይወት እንዲኖር የነበረውን ቅን ምኞት ተግባራዊ ለማድረግ በሚጥርበት ወቅት ውጤቱ የዘገየባቸው እናቶች በጥፊ ሲመቱት አባቶችም ሲሰድቡት አይተናል፤ ጎርባቾብ ግን ሁሉንም በትእግስት በመቀበል የለውጡን መንገድ ቢቀጥልም አድፍጠው የቆዩት የድርጅቱ አባላት ምቹ ጊዜ ጠብቀው ኩዴታ አካሄዱበት በዚህም አስታከው ሶቤት ህብረትን ለመበታተን ውስጥ ውስጡን ሲሰሩ የቆዩት የውጭ ሃይሎች በዴሞክራሲ ስም የስልጣን ጥም ያሰከራቸውን እነ ቦሪስ ይልሰንን በመጠቀም ሶቤት ህብረትን አፈረሰዋት፤ መቼም ይሄ ታሪክ በሃገራችን ላይ እንዲደገም የሚፈልግ ዜጋ አይኖርም እንዲያውም ይህ ችግር በእኛ ላይ ከመጣ ውጤቱ መቋጫ የሌለው ደም መፋሰስ እና አስነዋሪ ታሪክ ይሆናል።ስለዚህ ይህ የብዙ ሺ ወጣቶች ህይወት ተገብሮ የተጀመረ የለውጥ መንገድ ውጤታማ እንዲሆን በአካሄዳችን ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብናል፤ ለውጡ ለውጥ እንዲሆን በግለሰብም ሆነ በድርጅት የምንሰራቸው ስራዎች ለሁሉም የኢትዮጵያ ልጆች ዋስትና የሚሰጥ፤ ለብዙሃኑ ግልጽ እና ብዙሃኑን የሚያሳትፍ መሆን ይኖርበታል፤ ዛሬም የግለሰቦችን የስልጣን ጥም የድርጅቶችን አሻጥር መቋቋም ይኖርብናል፤ የኢትዮጵያን ህዝብ ሙብት እና ጥቅም በመርገጥ የግል እና የቡድን ፍላጎታቸውን ለማራመድ የሚፈልጉትን ሃይሎች ሁሉ በሁሉም መስክ ልንታገላቸው ይገባል። ደግሞም በድርጅት የታቀፈው የህብረተሰብ ቁጥር በጣም ዝቅተኛ መሆኑን እያወቅን ሁሉንም ነገር ለድርጅቶች ልንተውላቸው አይገባም፤ ትግሉ ውጤታማ እንዲሆን ሰፊ ህዝባዊ ተሳትፎ ይጠይቃል፤ የተለያዩ መድረኮችን በመፍጠር እራሳችን የመፍትሄው አካል ማድረግ አለብን;፤ ስለሆነም የኔ ድርሻ ምን መሆን አለበት ብለን እራሳችን በመጠየቅ ብሄራዊ ግዴታችን እንወጣ።